# የሥርዓት ቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት

መምህር ቸሬ አበበ

ሥርዓት የሚለው ቃል ሠርዐ ከሚለው የግዕዝ ቃል የወጣ ሲሆን ትርጉሜውም አሠራር፣ ሕግ፣ ደንብ፣ መርሐ ግብር ማለት ነው። ይህም ሥርዓት በክርስቶስ ደም የተመሰረተች ቤተ ክርስቲያን አምልኮቷን የምንትፈጽምበት፣ ሕዝበ እግዚአብሔርን የምትጠብቅበት ጸጋ የሚሰጥ ቅዱስ ሥርዓት ነው።

የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ለምእመናን የሃይማኖት ማጽኛ መሠረት እንዲሁም የቤተ ክርስቲያንና የሕዝበ እግዚአብሔር መለያም ነው። የቤተ ክርስቲያን እምነቷ ብቻ ሳይሆን ሥርዓቷም እግዚአብሔር በቅዱሳት መጽሐፍት የገለጠው ቅድስ ሥርዓት አምልኮ ነው። የአትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የዕለት ከዕለት መንፈሳዊ አገልግሎት የመትፈጽምበት የሥርዓት ቤተ ክርስቲያን መጻሕፈት አሏት። እነዚህን የሥርዓት መጻሕፈት ሐዋርያትና ሊቃውንት በየጊዜው ለቤተ ክርስቲያን መተዳደሪያ የወሰኑትን የደነገጉት ሕግ ነው።

*የሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ምንጮች:-*

1. የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት
2. የሐዲስ ኪዳን መጻሕፈት
3. የሊቃውንት መጻሕፈት
4. ቀኖናተ አበው /የአበው ቀኖናት/
5. የሥርዓት መጻሕፈት ወዘተ ናቸው።

ሥርዓትን መጠበቅና በሥርዓት መኖር አስፈላጊ እንደ ሆነ መንፈሳዊ ግዴታም እንዳለብን ዋነኛው የሥርዓት ምንጭ የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። ለምሳሌ ነቢዩ እግዚብሔር ኢሳይያስ «...ምድርም ከሚቀመጡባት በታች ረክሳለች፤ ሕጉን ተላልፈዋልና ሥርዓቱንም ለውጠዋልና።» /ኢሳ.24፥5/ በማለት ሕግና ሥርዓትን መጠበቅ እንዳለብን ይመክረናል።

ቅዱስ ዳዊትም /መዝ.118፥118/ ከሥርዓትዓ የሚርቁትን አንሳቀልካቸው በማለተት ከሥርዓት የተለየ ሰው በማንኛውም ሕይወቱ የተጉሳቆለ እንደሚሆን ነግሮናል። ከሐዲስ ኪዳንም ቅዱስ ጳውሎስ ያለ ሥርዓት የሚሄዱትን ገሥጿቸው። 1ኛ. ተሰ 5፥14። በተጨማሪም «ያለ ሥርዓት ከሚሄድ ወንድም ሁሉ ትለዩ ዘንድ በጌታችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እንለምናችኋለን» /2ተሰ.3፥6/በማለት የሥርዓትን አስፈላጊነትና ለሥርዓት ሊሰጥ የሚገባወን ክብር ገልጸልናል። የቅድስት ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሥርዓት መጻሕፍት በሐዋርያት ቅዱስ ሲኖዶስ የተደነገጉ ናቸው። ሲኖዶስ ማለትም ስብሰባ ወይም ጉባኤ ማለት ነው። ይህም ሐዋርያት ከክርስቶስ ዕርገትና ከርደተ መንፈስ ቅዱስ በኋላ ተሰብስበው የሠሯቸውና የደነገጓቸው ቀኖናት ናቸው።

## መጻሕፍቱ የተጻፉበት ቋንቋ

ስምንቱ የሥርዓት መጻሕፈት በመጀመሪያ የተጻፉበት እናት ቋንቋ ሱርስጥ /የሶርያ ቋንቋ/ ነው። አንዳንድ ሊቃውት ደግሞ በኋለኛው ዘመን እኒህን የሕግና የሥርዓት መጻሕፍት በየቋንቋው ለመተርጎም መነሻ ሆነው ያገለገሉት ሰነዶች በሙሉም ሆነ በከፊል ተጽፈው የተገኙት በግሪክ ቋንቋ ስለሆነ መጻሕቱ በመጀመሪያ የተጻፋት በግሪክ /ልሳነ ጽርዕ/ ነው ይላሉ። ሱርስጡንና ግሪኩን መሠረት በማድረግ ወደ ላቲን /ሮማይስጥ/፣ ግብጥ /ሳዲቅና ማምፌቲቅ/፣ ዐረብኛና ግእዝ ቋንቋዎች በተለያዩ ተርጓምያን ተተርጉመዋል። /ፍትሐ ነገሥት መቅድም/።

## የሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት አከፋፈል

ሐዋርያት የሠሯቸው የሐዲስ ኪዳን የሥርዓት መጻሕፍት ስምንት ሲሆኑ እነርሱም በአጠቃላይ በሦስት ይከፈላሉ። አከፋፈላቸውም እንደሚከተለው ነው።

1. መጽሐፈ ዲድስቅልያና አራቱ መጻሕፍተ ሲኖዶሳት /ትእዛዝ፣ግጽው፣ አብጥሊስና ሥርዓተ ጽዮን/:- ሐዋርያት በየጊዜው እየተሰበሰቡ ያዘጋጇቸው መጻሕፍት ናቸው።

2. ሁለቱ ኪዳናት /መጽሐፈ ኪዳን ቀዳማዊና ካልዕ/:- ጌታችን ከትንሣኤው በኋላ የተናገራቸው ናቸው::
3. መጽሐፈ ቀሌምንጦስ በሮም ኤጲስ ቆጶስነት ተሹሞ የነበረው የቅዱስ ጴጥሮስ ደቀ መዝሙር ቀሌምንጦስ የጻፈው መጽሐፍ ነው:: /ፊልጵ. 4፡3/::

በፍትሐ ነገሥት መጽሐፍ እንደ ተገለጠው የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ቁጥር 46 ሲሆኑ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ደግሞ ስምንቱ የትምህርትና የሥርዓት መጻሕፍትን ጨምሮ 35 ናቸው:: በአጠቃላይ የብሉይ ኪዳንና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ቁጥር 81 እንደ ሆነ የፍትሐ ነገሥት መተርጕሟንና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሊቃውንት ጉባኤ ያስረዳሉ::

## መጽሐፈ ትእዛዝ

ትእዛዝ ማለት በቁሙ ከሥራ አስቀድሞ የሚሰጥ፣ የሚጻፍ፣ የሚነገር፣ ሕግ፣ ሥርዓት ወይም አድርግ አታድርግ የሚል ፈቃድና ደንብ ነው:: መጽሐፈ ትእዛዝ ከሐዋርያት የሲኖዶስ መጻሕፍት አንዱ ክፍል ሲሆን ምልክቱ ወይም በአኅጽሮተ ቃል ልዩ መጠሪያው «ረስጠብ» በመባል ይታወቃል::
ትእዛዝ ሲኖዶስ ከ72 አንቀጾች በላይ ሲኖርት እነዚህም ስለ ሊቃነ ጳጳሳት ሥርዓት ሢመት አተገባበር፣ ስለ መሥዋዕት አቀራረብ፣ ስለ ንዋያተ ቅዱሳት ክብር፣ ስለ ሥርዓተ ጥምቀት፣ ስለ ሥጋ ወደሙ ክብር ወዘተ የሚናገር መጽሐፍ ነው::

## የመጽሐፈ ትእዛዝ አንቀጾች ዝርዝር ይዘት

ረስጠብ:- 1፣2 ስለ ሊቃነ ጳጳሳት አጠቃላይ ሥርዓት
ረስጠብ:- 3:- ስለ መሥዋዕትና የመሥዋዕት አቀራረብ ሥረዓት
ረስጠብ:- 4 ስለ ምሥጢረ ጥምቀትና ሥርዓተ ጥምቀት በተለይም ማንኛውም ተጠማቂ በሃይማኖት ከተለዩ ወይም ከተወገዙ ሰዎች ቢጠመቅ ክርስቲያን ሊሆን እንደማይችል
ረስጠብ:- 7 ሥርዓተ ፍትሐት እንዲገባ
ረስጠብ:- 8 ስለ ሊቃነ ጳጳሳት ሥርዓተ ሹመት
ረስጠብ:- 9 ሥልጣነ ክህነትን ስለ መጠበቅ
ረስጠብ:- 10 ካህናትን ማቃለልና መሳደብ እንደማይገባ
ረስጠብ:- 11 የዲያቆናትና የቀሳውስት የሥልጣነ ክህነት መቀበያ ጊዜ
ረስጠብ:- 13 ሁለት ያባ ካህን ሆኖ መሾም እንደማይገባው
ረስጠብ:- 17 ጠጉራቸውን ስለሚላጩ ሴቶች የተሰጠ ምክር
ረስጠብ:- 18 ወደ ዓለም ስለሚገቡ መነኮሳያት ንስሐ፣ ምክርና ተግሣጽ
ረስጠብ:- 19 ግብረ ሰዶም ስለሚፈጽሙ ሰዎች ንስሐ ስለ መስጠት
ረስጠብ:- 20 መናፍቃን ወደ ቤተክርስቲያን ከመመለሳቸው በፊት ቅዱሳት መጻሕፍትን ማንበብና መማር እንደሚገባቸው

ረስጠብ:- 21 ለቅድሳን ሰማዕታት መታሰቢያ እንደሚገባቸው
ረስጠብ:- 22 ምእመናን ከጠንቋዮችና ከአስማተኞች ጋር መተባበር እንደማይገባቸው
ረስጠብ:- 25 ልጅ ወልደው በድብቅ ስለሚገድሉ ዘማውያን ሴቶች
ረስጠብ:- 28 ወደ ቤተ ክርስቲያን የገባውንና የተቀደሰውን ንዋየ ቅዱሳት እንደገና ወደ ውጭ አውጥቶ ለሥጋ አገልግሎት ማዋል እንደማይገባ
ረስጠብ:- 30 ስለ ምስጢረ ቁርባን
ረስጠብ:- 33 ክርስቲያን ከጣዖት አምልኮ የተለየ ስለ መሆኑ
ረስጠብ:- 34-36 አንድ መናፍቅ ስለ እምነቱ ሲመለስ ስለሚፈጸምለት ሥርዓት
ረስጠብ:- 42 በስካርና በዘፈን ስሚገኝ ካህን ስለሚሰጠው ምክርና ስንብት
ረስጠብ:- 45 ስለ ሥጋ ወደሙ ክብርና አስፈላጊነት

ረስጠብ፡- 51 የካህናትና አርአያነትና አንዱ ካህን ያወገዘውን ሌላው ካህን መፍታት እንደማይችል

ረስጠብ፡- 53 ተሹሞ የሚያስተምርና የሚያስተዳድር ካህን ስለሚሰጠው ትምህርት፣ ምክርና ተግሣጽ

ረስጠብ፡- 54 የቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ የተቸገሩትን መርዳት እንደሚገባው

ረስጠብ፡- 57 ወላጆች ልጆቻቸውን በሃይማኖት ለማይመስሉቸው ማጋባት እንደሌለባቸው

ረስጠብ፡- 61 በአውሬ የተበላውንና የሞተውን የእንስሳ ሥጋ መብላት እንደማይገባ

ረስጠብ፡- 62 ከቀዳም ሥዑር በስተቀር ቅዳሜና እሑድን መጾም እንደማይገባ

ረስጠብ፡- 68 በቤተ ክርስቲያን የጸሎት ጊዜ የሊቀ ጳጳሱን ስም መጥራት እንዲገባ

ረስጠብ፡- 69 የሊቃነ ጳጳሳት ሥርዓተ ቀብርና አፈጻጸም

ረስጠብ፡- 73 ያለ ራሳቸው ፈቃድ ልጆችን ማጋባት እንደማይገባ

ረስጠብ፡- 81 ስለ መነኮሳትና ካህናት የአለባበስ ሥርዓት

ረስጠብ፡- 81-82 በዝሙት የወደቀ ካህን ከሥልጣኑ እንደሚሻር

## መጽሐፈ ግጽው

ከሠሯቸው ስምንት የሥርዓት መጻሕፍት አንዱ ነው። ሐዋርያት ለቀሌምንጦስ የሰጡት ሁለተኛ መጽሐፍ ነው። የዚህ መጽሐፍ መሪ ምልክት «ረስጠጅ» በመባል እንደሚታወቅ ፍትሐ ነገሥት ይናገራል። መጽሐፉ የእግዚአብሔር ህልውና በማስረዳት ጀምሮ ስለ ምሥጢረ ሥጋዌ፣ አጠቃላይ ኢየሱስ ክርስቶስ በኢየሩሳሌም ስለ ማስተማሩና ስለ ሠራቸው ሥራዎች ይናገራል፡፡ መጽሐፉ 27 ያህል አንቀጾች ያሉት ነው።

## የመጽሐፈ ግጽው ክፊል አንቀጾች በዝርዝር

ረስጠጅ 30፡- ስለ መሥዋዕትና አቀራረቡ ይናገራል።

ረስጠጅ 34፡- ጥምቀት በውኃ የሆነበትን ምሥጢር፣ የሐዲሳት አማንያን አጠማመቅ ሥርዓት፣ በተጨማሪም ወንድ ሴትን፣ ሴት ወንድን ክርስትና የሚያነሳ መሆኑን በሰፊው ያስተምራል።

ረስጠጅ 44፡- ያላመኑ ሰዎች፤ ለጥምቀት የልደረሱ አረማውያን ወይም ንዑስ ክርስቲያን ሥጋ ወደሙ እንዳይቀበሉ ይገዛል።

ረስጠጅ 46፡- ሥጋ ወደሙ ለመቀበል 18 ሰዓት ከምግብ መከልከል ወይም መጾም እንደሚገባ ያስረዳል።

## መጽሐፈ አብጥሊስ

አብጥሊስ የመጽሐፉ ስም ሲሆን ትርጉሙ ቀኖና ማለት ነው። መጽሐፈ አብጥሊስ የቅዱሳን ሐዋርያት ሲኖዶሳት መጽሐፍ ነው። 46 የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትንና 35 የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትን በአጠቃላይ 81 መጻሕፍትን ሙሉ ዝርዝር ይዞ ይገኛል። የአብጥሊስ መለያ መጠሪያው ወይም መሪ ምልክቱ «ረስጠአ/ረስጣ/» በመባል ይታወቃል። መጽሐፉ የሚናገረውም ስለ ኤጲስ ቆጶሳት፣ ስለ ካህናት፣ ስለ ዲያቆናትና ምእመናን አጠቃላይ የሥራ ድርሻና መንፈሳዊ ሕይወት በስፋትና ስለ ምስጢረ ንስሐ አሰጣጥና አተገባበር የሚያስረዳና የትምህርተ ሃይማኖትን፣ የሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን አስፈላጊነትና ምንነት የሚያትት ነው።

---

የሥርዓተ ቅዳሴው መጽሐፍ ከመዝ መሀሩነ ሐዋርያት በአብጥሊስሙ፡- ሐዋርያት በአብጥሊሳቸው እንዳስተማሩን /ረስጣ 8/ በማለት መጽሐፉ የሥርዓት መጽሐፍ መሆኑን ይጠቁማል። አብጥሊስ ሲኖዶስ አብጢሊሰ አፓስቶለስ፣ አፓስቶሊ ከሚለው የግሪክ ቃል የተወሰደ ሲሆን ተጥላሳት ከሚለው የዐረብኛ ቃል ጋር አንድ ነው። በመጽሐፈ ሲኖዶስ አብጥሊስ የሚነሳበት ርእስ «ሲኖዶስ ቀኖናተ ዘሐዋርያት ቅዱሳት ዘዜነወ ቀሌምንጦስ በእንተ ጴጥሮስ መምሩ ወይእቲ ትሰመይ አብጠሊሳት ውትልቆሙ 82 አብጠሊሳት፣ የቅዱሳን ሐዋርያት ሲኖዶስ እሷ ቀሌምንጦስ ስለ መምህሩ ጴጥሮስ የጻፉትና አብጠሊሳት ተብላ የምትጠራውና ቁጥራቸውም 82 የሆነ» የሚል ነው።

## የመጽሐፈ አብጥሊስ ዝርዝር ይዘት

ረስጣ 3:- ለእግዚአብሔር ንጽሕና የተለየ መሥዋዕት ስለ ማቅረብ
ረስጣ 4:- አሥራት በኩራት ቀዳምያት ማውጣት እንደሚገባ
ረስጣ 7:- ቀዳስያን ካህናት ሥጋ ወደሙን ሳይቀበሉ ማቀበል እንደማይገባቸው
ረስጣ 8:- ምእመናን ቤተ ክርስቲያን ገብተው ሥርዓተ ቅዳሴውን መከታተል እንደሚገባቸው
ረስጣ 9-19:- ምእመናን በካህናት ተወግዘው ከተለዩ ሰዎች ጋር መነጋገር እንደ ሌለባቸው
ረስጣ 13:- ካህናት የቤት ክርስቲያን አገልግሎት ትተው ለሥጋዊ ጥቅም ሌላ ቦታ መሄድ እንደማይገባቸው
ረስጣ 20:- አንድ ሰው በፈቃዱ ራሱን ጃንደረባ ቢያደርግ ራሱን ገድሏልና ሊሾም እንደማይገባው
ረስጣ 27:- ሥልጣነ ክህነትን በገንዘብ መቀበል እንደማይገባ
ረስጣ 30:- አንዱ ኤጲስ ቆጶስ የሻረውን ካህን ሌላው ኤጲስ ቆጶስ መመለስ እንደማይችል
ረስጣ 33:- ኤጲስ ቆጶስ በመማለጃ ሥልጣነ ክህነት መስጠት እንደማይገባው
ረስጣ 35:- ስለ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ
ረስጣ 37:- የቤተ ክርስተያን ንዋናየተ ቅድሳትን ካህናት መጠበቅ እንደሚገባቸው
ረስጣ 38-39:- የኤጲስ ቆጶስ ሀብት ከቤተ ክርስቲናያን ንዋያተ ቅድሳት ጋር መደባለቅ እንደማይገባ
ረስጣ 40:- በሥርዓተ ቁርባን ከመናፍቃን ጋር ኅብረት እንደሌለን
ረስጣ 43:- ባልን ወይም ሚስትን መፍታት በማያስችል ምክንያት መፍታት እንደማይገባ
ረስጣ 44-45:- ራስን ከፍ ከፍ ማድረግ እንደማይገባ
ረስጣ 48:- ምእመናን ከአመንዝሮችና ከዘማውያን ኅብረት ስለ መለየታቸው
ረስጣ 49-50:- ካህናት በበደል ብዛት የለዩት ሰው ከቤተ ክርስቲያን እንደሚለይ
ረስጣ 51:- መርዳት እንጅ በደካሞችና በበሽተኞች መሳቅና መሳለቅ እንደማይገባ
ረስጣ 53:- ኤጲስ ቆጶስ ሕዝቡን በሥርዓት ማስተዳደር እንደሚጠበቅበት
ረስጣ 54:- ኤጲስ ቆጶስ ድሆችን መርዳት እንዳለበት
ረስጣ 57:- ከሥጋዊ ፍርሃትና ጊዜያዊ ጥቅም የተነሣ ሃይማኖትን መካድ እንደማይገባ
ረስጣ 58:- ካህናት አውሬ የነከሰውንና የሞተውን እንስሳ ሥጋ መብላት እንደሌለባቸው
ረስጣ 59:- በዕለተ ሰንበት ጾም መጾምም፣ ማጾምም እንደማይገባ
ረስጣ 64:- በቤተ ክርስቲያን የተደነገጉ ዐበይት አጽዋማትን መጾም እንዲገባ
ረስጣ 66:- ከቤተ ክርስቲያን ውጭ ለሆኑ የማምለኪያ ቦታዎች መብዐ መላክ እንደማይገባ
ረስጣ 71:- አንድ ካህን ሹመቱን/ሥልጣኑን/ ለማንም ማውረስ እንደማይችል
ረስጣ 72:- የአካል ጉድለት /አንካሳነት፣ ዓይነ ሥውርነት/ ከሹመት እንደሚያስከለክሉ
ረስጣ 72-74:- ዕብድ፣ ጋኔን ያለበት፣ የማይሰማ ሰው ለሹመት እንደማይበቃ
ረስጣ 75:- አንድ ሰው ከአረማዊነት ወደ ክርስትና ከተመለሰ በኋላ ሥነ ምግባሩ መልካም ካልሆነ ሥልጣነ ክህነት እንደማይሰጠው።
ረስጣ 80:- የቅዱሳትም መጻሕፍት ቁጥር 81 ስለ መሆናቸው ወዘተ የሚሉ ዐበይት ነገሮች ያስገነዝቡናል።

---

## መጽሐፈ ሥርዓተ ጽዮን

ሥርዓተ ጽዮን ቀኖናተ ሐዋርያት ወይም ትምህርተ ሐዋርያት ከሚባሉት የሐዋርያት ሲኖዶስ መካከል አንዱ ነው። ሐርያት ለስብከተ ወንጌል ወደ ዓለም ከመላካቸው በፊት በጽርሐ ጽዮን ተሰብስበው ሠሩትና የደነገጉት የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት፣ ሕግና ትምህርት ነው። የሥርዓተ ጽዮን መጽሐፍ መጀመሪያ የተጻፈበት ቋንቋ ጽርዕ ሲሆን በኋላ ግን ወደ ዐረብኛና ወደ ግሪክ ቋንቋዎች ተተርጉሟል። «ሥርዓተ ጽዮን» የሚለው ቃል ሐዋርያት በጽርሐ ጽዮን እያሉ የሠሩት ሥርዓት ትምህርት ሲሆን ቃሉ የመጣው የመጀመሪያው ፊደል «ዓ» ከጽርዕ «ይን» ከጽዮን ወስዶ ከጽርሐ ጽዮን ሥርዓተ ጽዮን /ዓይን/ እንደተገኘ ይናገራል። በሌላ በኩል «ዓይን» ሐዋርያት ከተሰበሰቡበት የጽርሐ ጽዮን ሰገነት የመጀመሪያ ፊደል ነው ይባላል። የሥርዓተ ጽዮን መሪ ምልክቱ «ዓይን» ነው። የሥርዓተ ጽዮን ቀኖና መጽሐፍ የሚገልጸው ስለ በዓለ

አስተርእዮ /ኤጲፋንያ/፣ ስለ እሑድ ሰንበት በዓል አከባበር፣ ስለ ገሃድ ጾም ወዘተ ያትታል። የቀኖናቱ ብዛትም 30 የሚደርሱ ናቸው።

## የሥርዓት ጽዮን ቀኖናት ዝርዝር ይዘት

1. የሥርዓት ጽዮን ቀኖናትን ዝርዝር ይዘት በሦስት ልንከፍለው እንችላለን።
   - ቀኖና 1 ፊትን ወደ ምሥራቅ አዙሮ ስለ መጸለይ
   - ቀኖና 2-4 በዕለተ እሑድ፣ ረቡዕና ዓርብ ስለሚደረግ ጸሎት
   - ቀኖና 8-9 ስለ በዓለ ልደትና በዓለ ጥምቀት
   - ቀኖና 10 ስለ ዓቢይ ጾም
   - ቀኖና 11 ስለ በዓለ ዕርገት
   - ቀኖና 12 ስለ ቅዱስተ መጻሕፍት
   - ቀኖና 21 ስለ ቅዱሳን ስማዕታት መታሰቢያ
   - ቀኖና 28 ስለ ዘወትር ጸሎት
   - ቀኖና 30 ስለ ቅዱስ ቁርባን
2. የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ሥርዓት ድንጋጌዎች
   - ቀኖና 5 ስለ ቤተክርስቲያን ካህናት አገልጋዮች መዓረጋት
   - ቀኖና 7፣ 13 ስለ ዲያቆናት ካህናትና አስፈላጊነት
3. የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ሥነ ባሕርያት
   - ቀኖና 13 ስለ ሐሰተኛ ካህን የተሰጠ ትእዛዝ ቀኖና 15 ስለ ካህናትና ምእመናን ከከብ ቆጠራ መከልከል
   - ቀኖና 14፣20፣23፣26፣29 ስለቤተ ክርስቲያን አባላት ሥነ ባሕርያት
   - ቀኖና 27፣28 ስለ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያላቸውን ክብርና የተለየ ቦታ ይናገራል።

## መጽሐፈ ኪዳን

ኪዳን ማለት በቁሙ ውል፣ ስምምነት፣ የፍቅርና የአንድነት መሐላ፣ ሰላማዊ ሕግ፣ ትምህርት፣ ምስጋና ሁለቱን ወገን /እግዚአብሔርንና ሰውን ወይም ሰውንና ሰውን፣ አንድ የሚያደርግ ነው። ለሰው ረብና ጥቅም የሚሆን በተስፋ የቆሙ ቢጠብቁት በረከት የሚያስጥ ቢያፈርሱት ጉዳትና ጠብ የሚያመጣ ብዙ በረከት የሚያሳጣ ነው። መጽሐፈ ኪዳን የኢየሱስ ክርስቶስ የሐዋርያት ቃል ከትንሣኤ እስከ ዕርገት ያስተማራቸው እየጠየቁት የመለሰላቸው ነው። ይህንንም ከዕርገት በኋላ በጥንተ ስብከት ሐዋርያት ጽፈውታል።

ጌታ በመዋዕለ ሥጋዌ ሳለ ያስተማረው ወንጌል ሲባል ከትንሣኤው እስከ ዕርገቱ ያስተማረው ኪዳን ይባላል። ኪዳን የተባለበትም ምክንያት አብርሃምና ጌታ ሲነጋገሩት የነበሩትን ሲያጸና ዝንቱ ኪዳን ጽኑዕ ዘእም ኀበ እግዚአብሔር፡- ይህ ኪዳን በእግዚአብሔር ዘንድ የጸና ነው። በተማሪም እመቦ ዘዐቀበ ቃለ ዝንቱ ኪዳን የሐዩከመ መላእክት፡- ይህን የኪዳን ቃል የጠበቀ አንድ መላእክት ይኖራል በማለት በመጽሐፈ ኪዳን የተጠቀሰውን በሥርዓት ቅዳሴው ትርጉም የቅዳሴ እግዚእ መግቢያ ላይ ተጽፎ እናገኘዋለን። ከሞተ በኋላ በሥልጣኑ ተነሥቶ ስለ ምን ኪዳንን አስተማረ ቢሉ በመዋዕለ ሥጋዌው በፈቃዱ ለሰው ልጅ ድኅነት ወንጌልን እንዳስተማረ ከሞተም በኋላ ተነስቶ ለሰው ልጅ ሕይወት በፈቃዱ ኪዳንን አስተምሯል።

በጉባኤ ያስተማረው የትንሣኤ፣ አግብኦተ ግብር፣ የጥብርያዶስ የዕርገት ሲሆን ለአንድም ለሁለትም ሰው እየታየም አስተምሯል። መጻሕፍት ኪዳን የተባሉት ሁለት መጻሕፊት ሲሆኑ እነርሱም መጽሐፈ ኪዳን ቀዳማዊና መጽሐፈ ኪዳን ካልዕ ናቸው። እነዚህን መጻሕፍት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ከሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ጋር ቆጥራ የምትቀበላቸው የኪዳን መጻሕፍት ናቸው።

## መጽሐፈ ኪዳን ቀዳማዊ

«መጽሐፈ ኪዳን ዘእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ጸሐፍወ ለዝ ኪዳን ዮሐንስ ወጴጥሮስ ወማቴዎስ እንዘ ያጽሕፎሙ እግዚእነ ወፈነው በአርዓያዝ ግጽው እም ኢየሩሳሌም፣ ይህን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የኪዳን መጽሐፍ ዮሐንስ ጴጥሮስና ማቴዎስ ጌታችን እያጻፋቸው ጻፉት:: በዚህ ዓይነት መግለጫም ወደ ኢየሩሳሌም ላከው እንዲህ ብሎ በመጀመር የሚያትተው ይህ ጌታ ያስተማረው መጽሐፈ ኪዳን ቀዳማዊ ከ81 መጻሕፍት አንዱ ሲሆን የሚመደበውም ከሐዲስ ኪዳን ስምንት የትምርትና የሥርዓት መጻሕፍት ክፍሎች ነው::

መጽሐፈ ኪዳን ቀዳማዊ 29 አንቀጾች ያሉት መጽሐፍ ነው:: ይህም ስለ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን፣ የዘወትር ኪዳናት፣ ትምህርት ኅቡአት፣ እግዚአብሔር ዘብርሃናት፣ ቅዳሴ እግዚእ፣ በእንተ ቅድሳት ወዘተ የሚናገር መጽሐፍ ነው:: ይህ መጽሐፍ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከትንሣኤው በኋላ ከእርገቱ በፊት ለ11 ቅዱሳት ሐዋርያት በገሊላ ለ40 ቀናት እየተገለጠ ያስተማራቸው እየጠየቁት የመለሰላቸው ከሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት አንዱ ነው::
«ኪዳን ዘነገሮሙ እግዚእነ ለዐሠርቱ ወአሐዱ አርዳኢሁ በገሊላ እምድኅረ ተንሥአ እሙታን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ከተነሣ በኋላ ለዐሥራ አንዱ ሐዋርያት በገሊላ ጌታችን ያስተማራቸው /የነገራቸው/ የኪዳን መጽሐፍ ይህ ነው::» እንዲል:: /መጽሐፈ ኪዳን ቀዳማዊ ክፍል 1፣ ግብረ ሐዋ. 1÷2-3/::
የመጽሐፈ ኪዳን ቀዳማዊ ይዘት ሥርዓተ ጸሎትና ሥርዓተ ቅዳሴ ነው:: ይህም ጸሎት ኪደን እንዲጸልዩባቸው በተመደቡ ሦስት የኪዳን ጊዜያት /ጸሎተ ኪዳን ዘሠለስቱ ጊዜያት/ ተከፍለው የሚገኙ ዘጠኝ ሥርዓታት ጸሎታትን /ዘጠኙ ኪዳናት የሚባሉትን/ ይዟል:: እነርሱም፡-

1. ኪዳን ዘመንፈቀ ሌሊት
   ሀ. ለከ እግዚኦ ለገባሬ ኩሉ
   ለ. አምለከ ብርሃን ወላዴ ሕይወት
   ሐ. ንሤልስ ለከ ዘንተ ስብሐት
2. ኪዳን ዘነግህ
   ሀ. እግዚአብሔር አብ ወሃቤ ብርሃን
   ለ. እግዚኦ ኢየሱስ ክርስቶስ ስምዓነ ቅዱስ
   ሐ. ንሤልስ ለከ ቅዱስ ስብሐት
3. ኪዳን ዘሠርክ
   ሀ. ለከ ለአብ ዘኢይማስን መድኃኔ ነፍስነ
   ለ. ንዌድስከ እግዚኦ
   ሐ. ለከ ዘእምልበነ ናቸው::

## የመጽሐፈ ኪዳን ቀዳማዊ አንቀጾች ዝርዝር ይዘት፡-

አንቀጽ 1 ስለ መንፈስ ቅዱስ
አንቀጽ 2 ስለ ኋለኛው ዘመን ትምህርት
አንቀጽ 3 በስማያት ስላለው ነገር
አንቀጽ 4 ስለ ተመረጡ ሰዎች
አንቀጽ 5 ሀገሮች ላይ ስለ ተነገረ ትንቢት
አንቀጽ 6 ስለ ሐሳዊ መሲህ ትምህርት
አንቀጽ 7 ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያት ስላስተማራቸው ትምህርት
አንቀጽ 8 ኢየሱስ ክርስቶስ ለማርያም፣ ለማርታና ለስሎሜ ስለ መለሰላቸው
አንቀጽ 9 በሃይማኖትና በምግባር ስለ ጸኑ ሰዎች
አንቀጽ 10 ስለ ቤተ ክርስቲያን ቀኖና
አንቀጽ 11 ስለ ጳጳሳት ሹመት

አንቀጽ 12 ስለ ጳጳሳት ሹመት የሚደረግ ሥርዓተ ጸሎት
አንቀጽ 13 ኤጲስ ቆጶሳት ለጸሎትና ለመሥዋዕት ስለሚያደርጉት ዝግጅት
አንቀጽ 14 በቤተ ክርስቲያን ስለሚያስተምሩ ሰዎች
አንቀጽ 15 በቤተ ክርስቲያን የተለያየ መቋሚያ ቦታ ስለ መኖሩ
አንቀጽ 16 ስለ ሥርዓተ ቁርባን
አንቀጽ 17 ስለ ሥርዓተ ቅዳሴ
አንቀጽ 18 በሽተኞች ላይ ስለሚደረግ ቅብዕ
አንቀጽ 19 ስለ ማኅበር ምስጋና
አንቀጽ 20 ስለ ትምህርተ ኅቡአትና ኪዳን
አንቀጽ 21-22 ስለ ቀሳውስት ሹመትና ሥርዓተ ጸሎት
አንቀጽ 25 የካህናትን ቃል ስለሚሰሙ ሰዎች
አንቀጽ 26 ስለ ድኅነትና ስለ ጥፋት
አንቀጽ 27 በሽተኞችን ስለማጉበኙ ካህናት
አንቀጽ 28 ስለ ዲያቆናት ሹመት
አንቀጽ 29 ስለ ዲያቆናት መላክና እንግዳ መቀበል
አንቀጽ 30 ካህናት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዴት መቆም እንዲገባቸው
አንቀጽ 31 ስለ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት
አንቀጽ 32 ከቤተ ክርስቲያን ውጭ ስለሚቆሙ ሰዎች
አንቀጽ 33 ስለ ዲያቆናት አገልግሎት
አንቀጽ 34-36 ስለ ምእመናን ሹመትና ሲደረግላቸው ስለሚገባ ጸሎት
አንቀጽ 37 ስለ ጧት አገልግሎት
አንቀጽ 38 ስለ ንፍቀ ዲያቆን ሹመት
አንቀጽ 40 መሾም ስለ ሚገባው ሰው
አንቀጽ 41 ስለ ሕዝባውያን
አንቀጽ 42 አገልጋዮችን ስለ መቀበል
አንቀጽ 43 ስለ ዘማውያን ሠርዓት ጥምቀት
አንቀጽ 44 ሰላምን ስለ መቀበል
አንቀጽ 45 ሴቶች ራሳቸውን ስለ መከናነባቸው
አንቀጽ 46 ንዑስ ክርስቲያንን ስለ መባረክ
አንቀጽ 47-48 ንዑስ ክርስቲያንን በመከራቸው ጊዜ ስለ መቀበል
አንቀጽ 49 ስለ ሥርዓተ ጥምቀት
አንቀጽ 50 ስለ ሥርዓተ ጥምቀት
አንቀጽ 51 ስለ ምሥጢረ ቁርባን
አንቀጽ 52 በበዓለ ኀምሣ ጾምና ስግደት እንደማይገባ
አንቀጽ 53 ከኤጲስ ቆጶሳት ጋር ስለ ሚጠሩ ሰዎች
አንቀጽ 54 ለቤተ ክርስቲያን መበዓ ስለሚያገቡ ሰዎች
አንቀጽ 55 ስለ ሙሽሮች ሥርዓት
አንቀጽ 56 ለበሽተኞች ስለሚፈጸም ተግባር
አንቀጽ 57 ስለ ሞተ ድኻ ሰው ሚደረግ ሥርዓተ ጸሎት
አንቀጽ 58 ሁልጊዜ ስለሚጸልዩ ሰዎች
አንቀጽ 59 ስለ ሥርዓተ ቁርባን

### መጽሐፈ ኪዳን ካልዕ

ይህ ሁለተኛው የኪዳን መጽሐፍ ከስምንቱ የቅዱሳን ሐዋርያት የትምህርትና የሥርዓት መጻሕፍት አንዱ ሲሆን እንደ መጀመሪያው የኪዳን መጽሐፍ በአንቀጽ የተከፋፈለ አይደለም:: በሥርዓተ ቅዳሴው መጽሐፍ የቅዳሴ እግዚአ መግቢያ ላይ እንደ ተገለጸው መጽሐፈ ኪዳን ቀዳማዊ ባለ 59 አንቀጽ ሲሆን መጽሐፈ ኪዳን ካልዕ ደግሞ ወጥ ሆኖ ስለ ካህናት ሹመትና አገልግሎት፣ ስለ ንዑሰ ክርስቲያን ጥምቀትና ምሥጢረ ቁርባን እንዲሁም የጥጦስን የሐሳዊ መሲህን ነገር በመግለጽ ስለ ክርስቶስና ስለ ዳግም ምጽአት የሚናገር መጽሐፍ ነው::

ሐሳዊ ወሲሕ «እኔ ክርስቶስ ነኝ» ብሎ የሚመጣው አባቱ በነገደ ዔሳው እናቱ ከነገደ ዳን እንደሆነ የሚነገርለት የዓመፅና የክፋት ሰው ነው:: ኢየሱስ ክርስቶስ ሐሰተኞች ክርስቶሶችና ሐሰተኞች ነቢያት እንደሚነሱ ተናግሯል:: /ማቴ.11÷23-35፣24÷25/:: ሐሰተኞች ከራሳቸው አንቅተው ትንቢት እንናገራለን /ኤር 14÷14/ እያሉ በክፉ መንፈስ የሚመሩ /1ነገ 22÷19-24/ ራሳቸውንም ሌላውንም ወደ ጥፋት የሚወስዱ ናቸው:: ቅዱስ ዩሐንስም በደሴተ ፍጥምም በግዞት ሳለ በመንፈስ ቅዱስ የወደፊቱን የዓለም ጉዞ ምን እንደሚመስል በራእይ ሲመለከት ስለ ሐሳዊ መሲሕም በስፋት ተናግሯል:: /ራእይ 13÷1-18/:: በአጠቃላይ ይህ መጽሐፍ ስለ ሐሳዊ መሲሕና ተከታዮቹ በይበልጥ፣ በስፋት ይናገራል::

### መጽሐፈ ዲድስቅልያ

ዲድስቅልያ የመጽሐፉ ስም ሲሆን ትርጉሙም ትምህርት ማለት ነው:: ይህም ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን 35 የሐዲስ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝር ውስጥ አንዱና ጥንታዊው ነው:: ዲድስቅልያ ዘቅዱሳን ሐዋርያት /Apostalical constitutions/ ይባላል:: መጽሐፉ ቀደም ሲል ወደ ግእዝ ቋንቋ ተተርጉሞና ተጠብቆ ኖሯል:: እንዲያውም ከፍተኛ ዋጋው ቀደም ብሎ ስለታወቀ ከእንግሊዝኛ ትርጓሜው ጋር በአውሮፓ ታትሟል:: ይህ መጽሐፍ የቅዱሳን ሐዋርያት አስተምህሮ የሥርዓት ክፍል ሲሆን 43 አንቀጾችን የያዘ መድበለ ትምህርት ወተግሣጽ ነው:: እነዚህም ስለ ሰው ልጅ ሕይወትና ሞት ስለ ፍቅረ ሰብእና ፍቅረ እግዚአብሔር፣ ስለ ምሥጢረ ጥምቀት፣ ስለ ጾምና ጸሎት፣ ስለ ምሥጢረ ቁርባን፣ ስለ ካህናት ክብርና አገልግሎት፣ ስለ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስለሚፈጸሙ የተለያዩ ምሥጢራት ይናገራል::

መጽሐፈ ዲድስቅልያ ዐበይትና ንዑሳን አንቀጾች አሉት:: በእንዳንዱ ዐቢይ አንቀጽ ብዙ የተለያዩ ንዑሳን ክፍሎች ይገኛሉ::

### የመጽሐፈ ዲድስቅልያ

**ዐበይት አንቀጾች ዝርዝር**

አንቀጽ 1 ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት
አንቀጽ 2 ቅዱሳን መጻሕፍትን ማንበብና መረዳት እንዲገባ
አንቀጽ 3 የትዳር ጓደኞች መከባበር እንዲገባቸው
አንቀጽ 4 የካህናት ክብርና አገልግሎት
አንቀጽ 5 ኤጲስ ቆጶሳት ነገረ ሠሪን መስማት እንደማይገባቸው
አንቀጽ 6 ካህናት በፍቅር በየወሃት ሆነው ከኃጢአት ወደ ጽድቅ የሚመለሱትን ሰዎች ንስሐቸውን መቀበል እንደሚገባቸው::
አንቀጽ 7 አንድ ሰው መበደሉን ሳያረጋግጡ መቅጣት እንደማይገባ
አንቀጽ 8 ምእመናን ለቤተ ክርስቲያን መብዓ ማቅረብ እንዲገባቸው
አንቀጽ 9 ዲያቆናት ለካህናትና ለኤጲስ ቆጶሳት መታዘዝ እንዲገባቸው
አንቀጽ 10 ኤጲስ ቆጶሳት መንፈሳዊ ዕውቀትና ጥበብ ሊኖራቸው እንዲገባ
አንቀጽ 11 ቂም በቀል መያዝ እንደማይገባ
አንቀጽ 12 ክርስቲያኖች መዝፈንና ወደ ዘፈን ቦታ መሄድ እንደማይገባቸው
አንቀጽ 13 ባል የሌላቸው ባልቴቶች ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ማበርከት እንዲገባቸው
አንቀጽ 14 ሴቶች ማጥመቅ እንደማይገባቸው

አንቀጽ 15 ሥልጣነ ክህነት የሌለው የክህነትን ሥራ እንደማይሠራ

አንቀጽ 16 ባል ሚስትን ወይም ሚስት ባልን ያለ ምክንያት መፍታት እንደማይገባ

አንቀጽ 17 አባትና እናት ስለ ሞቱባቸው ልጆች

አንቀጽ 18 ኤጲስ ቆጶሳት አባትና እናት ስለ ሞቱባቸው ልጆች ማዘንና መርዳት እንዲገባቸው።

አንቀጽ 19 ባል የሞተባት ሴት በሃይማኖትና በትእግሥት መቀበል እንዲገባ

አንቀጽ 20 ኤጲስ ቆጶስ ሙበዓ ከማን መቀበል እንዲገባው ስለ መረዳቱ

አንቀጽ 21 ወላጆች ልጆቻቸውን መምከርና መገሠጽ እንዲገባቸው

አንቀጽ 24 ስለ ፋሲካ በዓል አከባበርና ስለ ዓበይት በዓላት ክብር እንዲገባ

አንቀጽ 25 ለቅዱሳን ሰማዕታት ክብር እንዲገባቸው

አንቀጽ 26 ክርስቲያኖች በቤተ ክርስቲያን ዘፈን ሳይሆን መዝሙር ማቅረብ እንዲገባቸው

አንቀጽ 27 ክርስቲያኖች በጣዖትና በአጋንንት ስማቸውን ይጠሩና ይምሉ ዘንድ እንዳይገባ

አንቀጽ 28 የበዓላትን ቀን በመንፈሳዊ ደስታ ማክበርና መጠበቅ እንደሚገባ

አንቀጽ 29 ሰሙነ ሕማማትንና የፋሲካ በዓላትን ማክበር እንደሚገባ

አንቀጽ 30 ወንጀለኞችና መናፍቃን ካልተመለሱ መለየት እንዲገባ

አንቀጽ 31 ጥንተ ጠላት ዲያብሎስ በቤተ ክርስቲያን ክርክርንና መለያየትን እንደሚፈጥር

አንቀጽ 32 ሐዋርያት ያስተማሩትን የአንድነት የሦስትነት ትምህርት ሃይማኖት መማር እንዲገባ

አንቀጽ 33 ለሞቱ ሰዎች መጸለይ እንዳይገባ

አንቀጽ 34 የሞትና የሕይወትን ጎዳና መለየት እንዲገባ

አንቀጽ 35 ስለ ሜሮን አስፈላጊነት

አንቀጽ 36 ስለ ቤተ ክርስቲያንና ስለ ሠራዊት መላእክት አገልግሎት

አንቀጽ 37 ስንበትን ሲያከብሩ ቅዱሳን መጻሕፍትን ማንበብ እንዲገባ

አንቀጽ 38 ይጠመቁ ዘንድ ስለሚወዱ ንዑስ ክርስቲያን

አንቀጽ 39 በውኃ ላይ ስለሚደገመው ጸሎት

አንቀጽ 41 አዲስ አማንያን ሲጠመቁ ጸሎት እንዲገባ

አንቀጽ 42 በሐዋርያት ሥልጣን ስለ ተሾሙ ኤጲስ ቆጶሳት

### መጽሐፈ ቀሌምንጦስ

ይህ መጽሐፍ ከቅዱሳት ሐዋርያት ስምንት የሥርዓትና የትምህርት መጻሕፍት አንዱ ነው። መጽሐፉም ሊቀ ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስ ስለ ገታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቴስ የተናገረውና ቅዱስ ቀለምንጦስ ከእርሱ አግኝቶ የጻፈው ነው። የቀሌምንጦስ መጽሐፍ በአጽሮተ ቃል ልዩ መጠሪያው ጴጥ. ሲሆን ትርጉሙም ጴጥሮስ ማለት ነው። ይዘቱም ሥርዓተ ቅዳሴያዊ ቅርጽ ያለው ነው። ሥርዓት ቅዳሰያዊ ቅርጹን አስመልክቶ ስለ ጽላተ ኪዳን ቡራኬ ማለትም በኤጲስ ቆጶስ አዲስ ቤተ መቅደስ የሚባረክበትን ሥርዓት፣ ሥርዓት ጥምቀትንና በእጅ መንሳና መተያያ ጥምቀት እንደማይፈቀድ ስለ ሥርዓተ ቁርባን ወዘተ ይናገራል። በቀኖናዊ ክፍሉም ስለ ሰማዕታትና ስለ ክብረ በዓላት፤ ስለ ሰንበተ ክርስቲያን የዕረፍት ቀን መሆን በሰሙነ ሕማማት የምእመናን ከተግባረ ሥጋ ማረፍ ግዴታ ስለ መሆኑ ያትታል። /ቀና.1-11/።

ቅዱስ ጳውሎስ ቀሌምንጦስ በፊልጵስዩስ ይኖር እንደ ነበርና «አንተም ደግሞ በሥራዬ አብረህ የተጠመድህ እውነተኛ ሆይ....» (ፊልጵ 4፥3) በማለት ቀሌምንጦስ በሕይወት መጽሐፍ የተጻፈ እውነተኛ የቅዱስ ጴጥሮስ ረድእና ደቀ መዝሙር እንደ ሆነ ገልጿል። በዚህ መጽሐፍ የአበው ሐዋርያት ትምህርቶች ከሆኑት ሁለት ጽሑፎች መልእክትና ድርሳን (Letter and Homily) ተጠቅሰዋል፤ በትውፊትም ይህ መጽሐፍ ቅዱስ ቀሌምንጦስ የሮማ 3ኛ ጳጳስ እንደነበረ ይናገራል።

ድኅረ ልደት ክርስቶስ የተጻፈው ቀዳማዊ ቀሌምንጦስ የቤተ ክርስቲያን አበው መምህራን በመገደላቸው ምክንያት አለመግባባት ወደ ተፈጠረባት የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን በሮማው ጳጳስ የተላከ መልእክት ነው። መልእክት ከሰባው

ሊቃናት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከተናገራቸውና እንዲሁም ከቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት በተለይ ከእብራውያን መልእክት የተወሰደ መሆኑ ተገልጿል::

ታሪክም «ሐዋርያው» ማትዮስ ለ40 ቀናት በእስር ቤት ተቀምጦ እግዚአብሔር ጽናቱን ስለ ሰጠው ያቀረቡለትን ሣር ሳይበላ በጾም አሳለፈው:: በ40ኛው ቀን ማትያስ ሣሩን ከፊቱ ከምሮ ሲዘምር እንድርያስ ከእግዚአብሔር ተልኮ በተዘጋው በር ገባ፤ በደስታና በናፍቆት ሰላምታ ከተሰጣጡ በኋላ «እንደ በጎች በተኩላዎች መካከል እልካችኋለሁ የሚለው ቃል ዛሬ በአንተ ተፈጸመ» ሲል የእግዚአብሔርን ቃል አስታወሰው፤ ከእስር ቤትም ይዞት ወጣ፤ አብረውት በዚያው ታስረው የነበሩ 183 ሰዎችም ወጡ:: ይህንን ተአምር ያዩት የአገሪቱ ሰዎች በትምህርቱ አምነው ተጠመቁ» በማለት ያስረዳል:: ለእነዚህ ሰዎች መጽሐፍ ጽፎ እንደሰጣቸው ቀሌምንጦስ በመጽሐፉ መስክሯል::

### የመጽሐፈ ቀሌምንጦስ ክፍሎች

መጽሐፈ ቀሌምንጦስ በስምንት ዓበይት ክፍሎች የሚከፈል ሲሆን የእያንዳንዱን ክፍል ሙሉ አሳብ ማቅረብ ባይቻልም በከፊል እንደሚከተለው ነው::

**ክፍል 1**

- መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከዐረገ በኋላ ሐዋርያትን በሁሉም አቅጣጫ እስከ ዓለም ዳርቻ ድረስ እንዲያስተምሩ እንደላካቸው፤
- ቤተ ክርስቲያን በሐዋርያት ትምህርት ላይ እንደ ተመሠረተች፤
- ከአዳም ጀምሮ ስላለው አጠቃላይ የዘር ሐረግ፤
- ስለ ገነትና ስለ ታላላቅ አባቶች የቀረበ ሰላምታ (ምስጋና)፤
- ከገነት ወጥተው ወደ ደብረ ቅዱስ ስለ ገቡ ሰዎች ሁኔታ

**ክፍል 2**

- ቀሌምንጦስ የቅዱስ ጴጥሮስ ደቀ መዝሙር ሆኖ ስለ መመረጡ
- ስለ ቀሌምንጦስ ሕይወትና አጠቃላይ ኑሮው
- የቀሌምንጦስ መንፈሳዊ አልግሎት

**ክፍል 3**

- ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ የኢየሱስ ክርስቶስን ማንነትና ለቅዱሳን ሐዋርያት የደረገውንና ያስተማረውን ሁሉ ለቀሌምንጦስ እንደ ነገረው፤
- በአገልግሎቱ እንዲጸና እንደ መከረው ይናገራል::

**ክፍል 4**

- እግዚአብሔር ለቅዱስ ጴጥሮስ ስላየው ራእይና ተአምራት፤
- ስለ ሥልጣነ ክህነት ከጳጳሳት እስከ ዲያቆና ት አጀማመርና አሰጣጥ፤
- ስለ ዓለም አፈጣጠርና ሁኔታ፤
- ስለ ዳግም ምጽአት እንዲሁም ስለ ጻድቃንና ኃጥአን ሁኔታ፤
- ስለ መንፈስ ቅዱስ መውረድና ሁሉን እንደሚገልጥላቸው ይናገራል::

ክፍል 5

- በሰው ልጆች ላይ በሰማይና በምድር ስለሚሆነው ነገር ሁሉ ቅዱስ ጴጥሮስ ለቀሌምንጦስ እንደ ነገረው
- ኢየሱስ ክርስቶስ በቤተልሔም ስለ መወለዱ፤
- ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ግብፅ ስለ መሰደዱ፤
- ኢየሱስ ክርስቶስ ግብፅንና በዙሪያዋ ያለ አወራጃዎችን ከአምልኮ ጣዖታት ነፃ ስለ ማድረጉ፤
- ወደ ገሊላ ስለ መግባቱ ይናገራል።

ክፍል 6

- እግዚአብሔር ለሙሴ የነገረው ሥርዓተ ደብተራ ኦሪት ለቅዱስ ጴጥሮስ እንደ ነገረው ቅዱስ ጴጥሮስ ደግሞ ለቀሌምንጦስ ይህን ሰማያዊ ሥርዓት እንዳስተማረው፤
- ሙሴ እንደ ሊቀ ጳጳሳት ሆኖ አሮንና ልጆቹን ስለ መሾሙ፤
- ቅዱስ ጴጥሮስ ለቀሌምንጦስ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን እንዳስተማረው፤
- ስለ ሙሴና ስለ ጴጥሮስ ንጽጽራዊ ትምህርት፤
- በክርስቶስ የሚያምን የክርስቶስን ሥራ እንደሚሠራ፤
- ቅዱሳን ሐዋርያት ድውያንን ስለ መፈወሳቸው፤
- ንጽሕና በረከት ለመቀበልም ለመስጠትም አስፈላጊ እንደሆነ፤
- ክርስቶስ ራሱን ለቤተ ክርስቲያን እንደ ሠዋ ይናገራል።

ክፍል 7

- ስለ ክርስቶስ አምላክነትና አዳኝነት፤
- ስለ ዲያብሎስ ክፋትና ሽንፈቱ፤
- ስለ ሙሴ በትርና ስለ ክርስቶስ መስቀል ምሳሌነት፤
- ስለ ቅዱሳን ሐዋርያት አስተምህሮ
- ኖኅ መርከብ እንዲሠራ ስለ መታዘዙ ይናገራል።

ክፍል 8

- ቅዱስ ጴጥሮስ ስለ ንስሐ አስፈላጊነት ያየውና ያስተማረው
- ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ብፁዕ ስለ መባሉ
- ቤተ ክርስቲያን በቅዱስ ጴጥሮስ የቃል መሠረትነት እንደምትሠራ
- ቅዱስ ጴጥሮስ የመንግሥተ ሰማያትን ቁልፍ ስለመቀበሉ ወዘተ ይናገራል።

## ማጠቃለያ

በአጠቃላይ ስምንቱ የሐዲስ ኪዳን የሥርዓት መጻሕፍት በይዘታቸው በትምህርትና በትንቢት በይበልጥም በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያነ ላይ ያተኩራሉ፡፡ እነዚህ የሥርት መጻሕፍት በተለያዩ አገሮች በተለያዩ ቋንቋዎች ተጽፈው የሚገኙ ቢሆንም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እስካሁን ድረስ ተጽፈው የሚገኙት በግእዝ ቋንቋ ነው፡፡ የሚገኙትም በታላላቅ ገዳማትና ጥንታውያን አድባርት ነው፡፡ በጽሑፉ እንደ ተገለጠው የሁሉም የሥርዓት መጻሕፈት አጠቃላይ ዝርዝር ይይዘታቸው አልተሟላም ይህም የሆነበት ምክንያት መጻሕፈቱ የሚገኙባቸው ቦታዎች ውስንነትና የቦታ ርቀት መኖር ነው፡፡ ከመጻሕፍቱ ብዙዎቹ በአንቀጾች የተከፋፈሉና ለእያንዳንዳቸው መሪ ምልክት ወይም ልዩ መጠሪያ እንዳላቸው ሊቃውንት ይናገራሉ፡፡ መጻሕፈትም ያረጋግጣሉ፡፡

ረስጠአ፡- የመጀመሪያዎቹ ሁለት ፊደላት «ረስ» - ረሰል (Rusul) ከሚለው ዐረብኛ ቃል የወጣ ሲሆን ትርጉሙም ሐዋርያት ማለት ነው፡፡ ሦስተኛው ፊደል «ጠ» ቀኖናቱ ወደ ምእመናን ሁሉ ከተላኩበት ረድእ ቀለምንጦስ ከሚለው ስም በማሳጠር የመጣ ነው፤ አንድም ተጣላሳት ከሚለው የዐረብኛ ቃል በማሳጠር የተወሰደ ሲሆን ቀኖናት፤ ትእዛዛት ማለት መሆኑ ተመልክቷል፡፡ «አ» በግብፃውያን አኀዝ አቆጣጠር ሥርዓት አንደኛ ቀደማዊ ማለት ነው፡፡ ረስጠአ ማለትም «ሐዋርያት ቀኖናት ቀሌምንጦስ ቀዳማዊ» ሲሆን ቅዱሳን ሐዋርያት በረድእ ቀሌምንጦስ አማካይነት የላኩት የመጀመሪያው የሥርዓት መጽሐፍ ማለት ነው፡፡

ረስጠብ፡- የ«ረስ» ና «ጠ» ትርጉም አስቀድሞ ከላይ እንደተገለጠው ነው፡፡ የመጨረሻው ፊደል «ብ» በግብፃውያን አኀዝ አቆጣጠር ሥርዓት የቀናቱን ቅደም ተከተለ የሚጠቁም ሲሆን ሁለቱኛው፤ ዳግማዊ ማለት ነው፡፡

ዓይን፡- ቃሉ የመጣው የመጀመሪያው ፊደል «ዓ» ከጽርዕ ዓይን ደግሞ ከጽዮን ወስዶ ከጽርሐ ጽዮን (ዓይን) እንደ ተገኘ ይናገራል፡፡ በሌላም በኩል ዓይን ሐዋርያት ከተሰበሰቡት ቦታ የጽርሐ ጽዮን በገነት የመጀመሪያው ፊደል ነው ይባላል፡፡

ድስቅ፡- ድስቅ ማለት የዲድስቅልያን መጽሐፍ የሚያስረዳ መሪ ምልክት /አኅጽሮተ ቃል/ ነው፡፡
ቀሌ/ጴጥ፡- ቀሌ. ማለት ቀሌምንጦስ ማለት ሲሆን ጴጥ. ማለትም የቀሌምንጦስ መጽሐፍ አኅጽሮተ ቃል ሆኖ ጴጥሮስ ማለት ነው፡፡ ይህም ቅዱስ ጴጥሮስ እየነገረው የጻፈው መሆኑን የሚያስረዳ ነው፡፡

**ወስብሐት ለእግዚአብሔር**

——————//——————